የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፷፯
አዲስ አበባ መስከረም ፳፫ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 67
ADDIS ABABA 3rd October 2013

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፺፮/፪ሺ፭ ዓ.ም.
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እውቅና፣ የአቻ ግምት፣ የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ......ገጽ ፯ሺ፩፻፬
ሠንጠረዥ ......ገጽ ፯ሺ፩፻፮

CONTENTS

Regulation No. 296/2013
Service Fees for Accreditation of Higher Education Institutions, Equivalence of Qualification , Authentication of Educational Certificate and Related Services Council of Ministers Regulation...... Page 7104
Schedule ...... Page 7106

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፮/፪ሺ፭

## ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እውቅና፣ ለአቻ ግምት፣ የትምህርት ማስረጃን ለማረጋገጥና ተያያዥ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚከፈለውን የአገልግሎት ክፍያ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ቲግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰//፪ሺ፩ አንቀጽ ፲፯(፩) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እውቅና፣ የአቻ ግምት፣ የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፮/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፩/፪ሺ፬ የተቋቋመው የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 296/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE SERVICE FEES FOR ACCREDITATION OF HIGHER EDUCATION INSTITUTIONS, EQUIVALENCE OF QUALIFICATION , AUTHENTICATION OF EDUCATIONAL CERTIFICATE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 17(1) of the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 648/2009.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Service Fees for Accreditation of Higher Education Institutions, Equivalence of Qualification, Authentication of Educational Certificate and Related Services Council of Ministers Regulation No. 296/2013".

### 2. Definitions

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Agency" means the Higher Education Relevance and Quality Agency established by Council of Ministers Regulation No. 261/2012;

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፪/ "የእውቅና ፈቃድ" ማለት የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ለመጀመር በአዋጁ መሰረት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው፤

፫. "የእውቅና እድሳት ፈቃድ" ማለት የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና እንዲቀጥል ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጥ የፈቃድ እድሳት ነው፤

፬. "አቻ ግምት" ማለት ከውጭ አገር ለተገኘ የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃ ከአገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃ ጋር በማነጻጸር ደረጃ መስጠት ነው፤

፭/ "የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥ" ማለት እውቅና ከተሰጠው የአገር ውስጥ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተገኘን በማናቸውም ሰው የቀረበን የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ ነው፤

፮/ "ድንበር ዘለል ድህረ ምረቃ ትምህርት" ማለት በውጭ አገር የሚገኝ አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከአገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት አቅራቢ ጋር በመተባበርም ሆነ ያለትብብር ኢትዮጵያ ውስጥ በድህረ ምረቃ የሚሰጠው ከፍተኛ ትምህርት ነው፤

፯/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፰/ "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ ነው፤

፱/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ስር የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

፲/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. ስለ አገልግሎት ክፍያ

፩/ ለእውቅና ፈቃድ የሚፈፀም የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አንድ በተመለከተው ተመን መሠረት ይፈፀማል፡፡

፪/ ለአቻ ግምት የሚፈፀም የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሁለት በተመለከተው ተመን መሠረት ይፈፀማል፡፡

፫/ የትምህርት ማስረጃን ለማረጋገጥ የሚፈፀም የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሦስት በተመለከተው ተመን መሠረት ይፈፀማል፡፡

፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መስከረም ፳፫ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር



2/ "accreditation" means license issued for higher education institution to start higher education and training;

3/ "renewal of accreditation" means renewal of license issued for higher education institution to continue higher education and training;

4/ "equivalence of qualification" means standardizing a higher educational qualification given by a foreign institution by comparing with domestic higher educational qualification;

5/ "authentication of certificate" means certifying higher education qualification obtained from locally accredited higher education institution submitted by any person;

6/ "cross-border post graduate study" means post graduate study provided by foreign higher institution in Ethiopia in collaboration with local higher education provider or alone;

7/ "person" means any natural or juridical person;

8/ "Proclamation" means the Higher Education Proclamation No.650/2009;

9/ definitions provided under the Proclamation shall be applicable to this Regulation;

10/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. **Service Fees**

1/ The service fees for accreditation shall be at the rate prescribed in Schedule One attached hereto.

2/ The service fees for equivalence of qualification shall be at the rate prescribed in Schedule Two attached hereto.

3/ The service fees for authentication of certificates shall be at the rate prescribed in Schedule Three attached hereto.

4. **Effective Date**

This Regulation shall come in to force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of October, 2013

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL

DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## ሠንጠረዥ አንድ

## የእውቅና ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ለመጀመሪያ ዲግሪ | ለማስተርስ | ለፒኤችዲ |
| ፩ | የመደበኛና የርቀት የአገር በቀል የቅድመ ምረቃ እና ድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች | | | |
| ፩.፩ | እስከ ሁለት መርሃግብሮች የእውቅና ፈቃድ | ፬ሺ | ፯ሺ | ፲ሺ |
| | ለእያንዳንዱ ተጨማሪ መርሃግብር | ፩ሺ | ፫ሺ፭፻ | ፭ሺ |
| ፩.፪ | እስከ ሁለት መርሃግብሮች የእውቅና ፈቃድ እድሳት | ፭ሺ | ፰ሺ | ፲፩ሺ |
| | ለእያንዳንዱ ተጨማሪ መርሃግብር | ፪ሺ | ፬ሺ | ፭ሺ፭፻ |
| ፩.፫ | በድጋሚ ለሚቀርብ የእውቅና ፈቃድ በእያንዳንዱ መርሃግብር | ፪ሺ | ፫ሺ | ፬ሺ፭፻ |
| ፩.፬ | በድጋሚ ለሚቀርብ የእውቅና ፈቃድ እድሳት በእያንዳንዱ መርሃግብር | ፪ሺ፭፻ | ፫ሺ፭፻ | ፭ሺ |
| ፩.፭ | ስርዓተ ትምህርት በድጋሚ ሲገመገም ለእያንዳንዱ መርሃግብር | ፩ሺ | ፩ሺ፯፻፶ | ፪ሺ፭፻ |
| ፩.፮ | የርቀት ትምህርት ዕውቅናና ድጋሚ ዕውቅና ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ማዕከል | ፩ሺ | ፪ሺ፭፻ | - |
| ፪ | ድንበር ተሻጋሪ የድህረ ምረቃ ትምህርት | | | |
| ፪.፩ | ለአንድ መርሃግብር የእውቅና ፈቃድ | | ፲ሺ | ፲፭ሺ |
| ፪.፪ | ለአንድ መርሃግብር የእውቅና ፈቃድ እድሳት | | ፲፪ሺ | ፳ሺ |
| ፪.፫ | ለአንድ መርሃግብር በድጋሚ ለሚቀርብ የእውቅና ፈቃድ | | ፭ሺ | ፯ሺ፭፻ |
| ፪.፬ | ለአንድ መርሃግብር በድጋሚ ለሚቀርብ የእውቅና ፈቃድ እድሳት | | ፮ሺ | ፲ሺ |

## SCHEDULE ONE

## FEES FOR ACCREDITATION

| No. | Type of Service | Amount of Fees in Birr | | |
|---|---|---|---|---|
| | | First Degree | Masters | Ph.D |
| 1 | Regular and Distance local Undergraduate and Postgraduate Programs | | | |
| 1.1 | Accreditation up to two programs | 4000.00 | 7000.00 | 10000.00 |
| | For each additional program | 1000.00 | 3500.00 | 5000.00 |
| 1.2 | Renewal of accreditation up to two programs | 5000.00 | 8000.00 | 11000.00 |
| | For each additional program | 2000.00 | 4000.00 | 5500.00 |
| 1.3 | Reapplication of accreditation for each program | 2000.00 | 3000.00 | 4500.00 |
| 1.4 | Re-application of renewal of accreditation for each program | 2500.00 | 3500.00 | 5000.00 |
| 1.5 | Re-evaluation of curriculum for each program | 1000.00 | 1750.00 | 2500.00 |
| 1.6 | Accreditation/reaccreditation of distance programs for each branch center | 1000.00 | 2500.00 | - |
| 2 | Cross Border Post Graduate Studies | | | |
| 2.1 | Accreditation for one program | | 10000.00 | 15000.00 |
| 2.2 | Renewal of accreditation for one program | | 12000.00 | 20000.00 |
| 2.3 | Re-application of accreditation for one program | | 5000.00 | 7500.00 |
| 2.4 | Renewal for reaccreditation for one program | | 6000.00 | 10000.00 |

## ሠንጠረዥ ሁለት
## የአቻ ግምት አገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር | |
|---|---|---|---|
| | | ለኢትዮጵያ ውያን | ለውጭ ዜጎች |
| ፩ | ከውጭ አገር ዲግሪና ከዚያ በላይ ይዘው ለሚ መጡ ለአቻ ግመታ አገ ልግሎት | ፪፻፳፭ | ፬፻፶ |
| ፪ | ምትክ ለሚሰጥ አቻ ግመታ | ፩፻ | ፪፻ |
| ፫ | በጊዜያዊነት ለሚሰጥ አቻ ግመታ | ፩፻፳፭ | ፪፻፶ |
| ፬ | ከውጭ አገር የትምህ ርት ማስረጃ ይዘው መማር ለሚፈልጉ የሚ ሰጥ ማረጋገጫ | ፩፻፶ | ፫፻ |

## SCHEDULE TWO
## FEES FOR EQUIVALENCE OF QUALIFICATION

| No. | Type of Service | Amount of Fees in Birr | |
|---|---|---|---|
| | | For Nationals | For Foreigners |
| 1 | Equivalence of foreign Bachelor and above degrees | 225.00 | 450.00 |
| 2 | Replacement of equivalence | 100.00 | 200.00 |
| 3 | Provisional Equivalence | 125.00 | 250.00 |
| 4 | Providing "To Whom it may Concern" letter for foreign certificates for further education | 150.00 | 300.00 |

## ሠንጠረዥ ሦስት
## የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥ አገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር | |
|---|---|---|---|
| | | ለኢትዮጵያ ውያን | ለውጭ ዜጎች |
| ፩ | ኦሪጅናል ዶክመንት ለማረ ጋገጥ | ፪፻ | ፬፻ |
| ፪ | ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ኮፒ | ፶ | ፩፻ |
| ፫ | ተቋሙ እውቅና ያለው ስለመሆኑ ለሚመለከተው ሁሉ በሚል የሚሰጥ አገል ግሎት | ፩፻ | ፪፻ |
| ፬ | ተቋሙ እውቅና ያለው ስለ መሆኑና ሌሎች መረጃዎች በውጭ ለሚገኙ ተቋማት በቀጥታ ሲላክ | ፩፻፸ | ፫፻፵ |

## SCHEDULE THREE
## FEES FOR AUTHENTICATION OF CERTIFICATES

| No. | Type of Service | Amount of Fees in Birr | |
|---|---|---|---|
| | | For Nationals | For Foreigners |
| 1 | Authentication of original documents | 200.00 | 400.00 |
| 2 | For each additional copy | 50.00 | 100.00 |
| 3 | Providing "To Whom it may Concern" letter that ascerta ins the institution is accredit ed | 100.00 | 200.00 |
| 4 | Sending of letters to foreign institution upon request, certifying that the institution is accredited | 170.00 | 340.00 |